# የማሽከርከር ስነ-ባህሪ

የምንሰጣቸው አገልግሎቶች

- በግል እናስጠናለን
- ስለመንጃ ፈቃድ እናማክራለን
- የፈተና ጥያቄዎችን በግል እናሰራለን


መርዕድ በሻህ

0968573578

0961152483

## መሰረታዊ የማሸከርከር ስነ-ባህሪ ኃሳቦችና ጉዳዮች

ይህ ምዕራፍ ከማሸከርከር ስነ-ባህሪ ጋር የሚገናኙ ጉዳዮችን ያብራራል። እንነዲሁም የአሽከርካሪ ሙያዊ ስነ-ምግባርን ይተነትናል። በመጨረሻም የአሽከርካሪ ኃላፊነትና ተግባርን ይገልፃል።

## ባህሪ

- የአስተሳሰብ፤አመለካከት፡እውቀት፤ችሎታ፤ስሜት፤ተነሳሽነት እና ማንኛው ድርጊት ማለት ነው፡፡በቀጥታ ሊቃኝ ሊመዘገብና ሊለካ የሚችል ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ሊታወቅ የሚችል ነገር ነው፡፡

## ስነ-ባህሪ

- ባህሪና የአእምሮ አስተሳሰብ ሂደትን የሚያጠና ሳይንስ ነው፡፡ የሰዎችንና የእንስሳትን ባህሪ የሚያጠና ሳይንስ ነው፡፡

## አካባቢና ተፈጥሮ በባህሪ ላይ ያላቸው ሚና

- የሰው ልጅ ባህሪይ የውርስና የአካባቢ የጋራ ውጤት ነው ፡፡

# የማሽከርከር ስነ-ባህሪ

አሽከርካሪዎች በሚያሽከረክሩ ወቅት የሚያሳዩትን ባህሪ የሚያጠና የስነ-ባህሪ ዘርፍ ነው፡፡

# ከሌሎች መንገድ ተጠቃሚዎች ጋር በትብብር መንፈስ መስራት

- ትእግስት ማድረግ
- ትኩረት መስጠት
- ሌሎችና እና ራስን ከአደጋ መከላከል
- ጠንቃቃና አስተዋይ መሆን
- ግዴለሽነትን ማስወገድ
- በሃላፊነት ጉድለት ህይወት ያለው ነገር እንዲጠፋ አይፈልጉም
- ቅድሚያ የመስጠት ባህሪን ማዳበር
- የመንገድ ምልክትን ዘወትር ማሰብ
- ቅድሚያ ለሚሰጡ ምልክቶች ተገዢ መሆን

# የማሽከርከር ስነ-ባህሪ ጉዳዮች

# 1.ዝግጁነት

ብስለት፤የችሎታ፤የትምህተና የመነሳሳት የጋራ ውጤት ነው፡፡የዝግጁነት መገለጫዎች ውስጥ ሊጤኑ የሚገባቸው ነገሮች፡-

- ለማሽከርከር ጤነኛ መሆናችንን ማረጋገጥ
- የተሽከርካሪ ክፍሎችን በአግባቡ መፈተሽ
- የመንገድ፤የአየርና የትራፊክ ሁኔታዎችን ማጤን

## 2. መነቃቃት/መነሳሳት

- ባህሪን ወደ ግብ የሚያንቀሳቅስ ሂደት ነው፡፡

# 3. መረጃ የመሰብሰብና የመተርጎም ሂደት

# ሀ. መገንዘብ/መስማት/

በስሜት ህዋሳቶቻችን አማካኝነት የሚመጡ መረጃዎችን የመቀበልና ወደ አእምሮ የመላክ ሂደት ነው፡፡

- በማየት፡-ከ80% - 90% አከባቢን ለማወቅ ይረዳል
- በመስማት
- በማሽተት
- በመዳሰስ

# ለ.ትኩረት

በስሜት ህዋሳቶቻችን አማካኝነት ከሚደርሱ መረጃዎች ዋናውና ተፈላጊውን የመምረጥ ሂደት ነው፡፡

# ሐ.ማስተዋል

በስሜት ህዋሳቶቻችን አማካኝነት የመጣን መረጃ የማቀናበርና ትርጉም  የመስጠት ሂደት ነው፡፡

# የባህሪ መለዋወጥ መንስኤዎች

- አከባቢ፡- የምንኖርበት አከባቢ እያንዳንዱ ነገር በኛ ዙሪያ የተሰራ ነው፡፡
- ቤተሰብ፡- ከቤተሰብ የወረስናቸው አመለካከት፡አስተሳሰብና ተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ አስተዋጾ አላቸው፡፡
- አካላዊ ሁኔታ:- በሚደክመንና በሚያመን ግዜ የባህሪ መለዋወጥ ሊታይ ይችላል
- ኃይለ ስሜት፡- ፍላጎትን፤ፍቅርን፤ጥላቻን፤ሀዘንን፤ንዴትን ይገልጻል፡፡
- ስልጠና:- የሰው ልጅ በሰለጠነበት ሙያ የባህሪ ለውጥ ማምጣት ያስችለዋል፡፡የአሽከርካሪዎችን ባህሪ በስልጠና መቀየር ይቻላል፡፡

# የማሽከርከር ሙያዊ ስነ-ምግባር

**ሙያ**

- የአሽከርካሪነት ሙያ በትምህርትና ሥልጠና የተገኘውን ዕውቀት፣ክህሎትና አስተሳሰብን በመጠቀም ለህብረተሰቡ ተገቢውን አገልግሎት መስጠት የሚያስችል የስራ መስክ ነው፡፡

ስነ-ምግባር

- መልካምና መጥፎውን ለመለየት የሚያስችል መጥፎውን በመተው መልካም ነገርን ብቻ እንድናደርግ የሚያበረታታ እሴት ነው፡፡ አብሮ የመስራትና አብሮ የመኖር እሴት ነው፡፡

# ሙያዊ ስነ-ምግባር

- ማለት ባለሙያው በተሰማራበት ሙያ የሚሰራው ስራ ውጤታማ እንዲሆን እንደተሰማራበት የሙያ አይነት አባላቱ በጥብቅ መከተል የሚገባቸውን መርሆችና ስነ-ስርዓቶችን ያመለክታል፡፡

# የማሽከርከር መርሆች

- የመንገድ ደህንነትና የትራንስፖርት ሰላማዊ እንቅስቃሴን በሚመለከት ወሳኝ ሚና የሚጫወተው አሽከርካሪው እንደመሆኑ መጠን በጥንቃቄ የማሽከርከር ኃላፊነት አለባቸው፡፡
- አሽከርካሪዎች የራሳቸውን ህይወት ብቻ መጠበቅ ሳይሆን የሌሎችን ህይወትና ንብረት የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው፡፡
- በአሽከርካሪዎች ስህተትና በቴክኒክ ጉድለት ከሚደርሱ አደጋዎች የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው፡፡
- አሽከርካሪዎች ባለማወቅ፣ በቸልተኝነትና ስነ-ስርዓት በጐደላቸው አሽከርካሪዎችና እግረኞች ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎችን አስቀድሞ የመጠንቀቅ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## ሙያዊ ስነ-ምግባራቸውን አክብረው የሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች ተጋባራቶች

- ከነዱ አይጠጡ ከጠጡ አይንዱ
- ያለ ሐኪም ትዕዛዝ ከባድ መድሀኒት ወስደው አያሽከረክሩም
- ያለምንም እረፍት ከአራት ሰአት በላይ አያሽከረክሩም
- የእንቅልፍ ስሜት በተሰማቸው ግዜ ሙሉ እረፍት ይወስዳሉ
- ስለጉዞዋቸው እቅድ ያወጣሉ
- የመኪናቸውን ጠቅላላ አካል ይጠብቃሉ
- የተሳፋሪው ደህንነት የአሽከርካሪው ኃላፊነት መሆኑን ይገነዘባሉ
- ለማሽከርከር አስቸጋሪ በሆነ መንገድ ላይ አያሽከረክሩም

- መታጠፊያ መንገዶች ላይ ብረቱ ጥንቃቄ ያደርጋሉ
- የአየር ሁኔታ መጥፎ ሁኔታ ላይ ከተገኘ የተሸለ እስኪመጣ አያሽከረክሩም
- ሌሎችንና እራሳቸውን ከአደገኛ ሁኔታዎች ይከላከላሉ
- ረጅም የግንባር መብራት በአግባቡ ያበራሉ
- ለእግረኛ ቅድሚያ ይሰጣሉ
- በእነርሱ ኃላፊነት ጉድለት ህይወት ያለው ነገር እንዲጠፋ አይፈልጉም
- የማሽከርከር ሙያ ብቃታቸውን ከፍ ለማድረግ ይጠራሉ
- የፍጥነት ገደቡን ያከብረራሉ

- ለትራፊክ መብራት ተገቢውን ምላሽ ይሰጣሉ
- የመንገድ ምልክቶችንና ትዕዛዞችን ያከብራሉ
- የትራፊክ ፖሊሶችን ተዕዛዝ ያከብራሉ
- የጉዞ እቅድ ያወጣሉ
- የራሳቸውንና የሌሎችን ደህንነት ለመጠበቅ ቁርጠኛ ናቸው
- ሙያዊ ስነ-ምግባር አላቸው
- ለመንገድ ህግጋት ይገዛሉ.......ወ.ዘ.ተ.

# አልኮል መጠጥ ጠጥቶ ስለማሽከርከር

# አልኮል

- የመደበት ተጽእኖ ያሳድራል
- የአእምሮ ሚዛንን/የነርቭ ስርዐት ያዛባሉ
- የማየት ችሎታን ይቀንሳል
- የማተኮር ችሎታን ይቀንሳል
- የመገንዘብ ችሎታን ይቀንሳል
- ቅልጥፍናን  ይቀንሳል

## አልኮል ጠጥተው የሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊታወቁ ይችላሉ

- በጣም በዝግታ ወይም  በጣም በፍጥነት ያሽከረክራሉ
- በተሳሳተ የመንገድ መስመር ውስጥ ገብተው ያሽከረክራሉ
- መሪ በማወላወል ያሽከረክራሉ
- መታጠፊያ ላይ በፍጥነት ያዞራሉ
- ፍሬቻ መብራት ሳያበሩ ይዞራሉ
- መብራት ሳያበሩ ያሽከረክራሉ
- የትራፊክ መብራትና  የሚያስቆሙ ምልክቶችን ይጥሳሉ
- ከልክ ባለፈ ፍርሀት ውስጥ ተውተው ያሽከረክራሉ

# የአልኮል መጠጥ በጠጡ ወቅት

- የህዝብ ትራንስፖርት ወይም ታክሲ መጠቀም፣
- ሌላ አሽከርካሪ ማለትም አልኮል መጠጥ ያልወሰደ እንዲያሽከረክር ማድረግ፣
- የጠጡበት ቦታ ማደር፣
- ሌላ አሽከርካሪ እንዲያደርስዎት ስልክ ደውለው መጥራት፣
- የአልኮል መጠጥ መጠጣት አስፈላጊ መስሎ ከታይዎት ከቤተሰብና ከጓደኞችዎ ጋር በመኖሪያ ቤት ለመጠጣት መሞከር፡፡

# የአልኮል የተሳሳተ አመለካከት

- አልኮል የማሽከርከር ችሎታ ይጨምራል
- አንዳንድ ሰዎች አልኮል ቢጠጡም ተጽዕና አያሳድርባቸውም
- ከተበላ በኃላ ቢወሰድ አያሰክርም
- ቡናና ትንሽ ንጹ አየር ስካርን ይቀንሳል
- ቢራ የወይንን ወይም የውስኪን ያህል የአልኮልነት ይዘት የለውም

# የአልኮል እውነታዎች

- የንቃት ችሎታን በመቀነስ ለአደጋ ያጋልጣል
- አልኮልን የጠጣ ሰው ሁሉ ተጽእኖውን መቋቋም አይችሉም
- ምግብ የአልኮል ተጽዕኖ ቢቀንስም ጨርሶ አያጠፋውም
- በየትኛውም መንገድ ስካርን መቀነስ አይቻልም
- ቁጥሩ አነስተኛ የሆነ ቢራ የተወሰኑ ብርጭቆዎችን ያህል ውስኪ ወይም ወይን ያህል ጠንካራ ነው፡፡

# የአልኮል መጠጥና ህግ

- የትራንስፖርት ህግና ደንቦች የትራፊክ አደጋን ለመከላከልና አሽከርካሪች በመንገድ ላይ በስርዓት እንዲንቀሳቀሱ ትዕዛዝ ያስተላልፋሉ፡፡ እነኝህን ህግና ደንቦች የተላለፈ አሽከርካሪ ማንኛውንም  የትራንስፖርት እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር በወጣ አዋጅ መሰረት ይቀጣል፡፡
- አሽከርከሪች ሊያውቋቸው ከሚገቡ ልዩ ልዩ የትራንስፖርት ደንቦችና ህጐች መካከል አንዱ በአልኮል መጠጥ፣ በመድሃኒት ወይም በአደንዛዥ ዕፅ ተመርዞ ማሽከርከር ክልክል መሆኑን የሚገልፅ ነው፡፡ ስለሆነም አልኮል መጠጥ ጠጥቶ ማሽከርከር በህግ የሚያስጠይቅና የሚያስቀጣ መሆኑን ተረድቶ በጠጡ ወቅት ያለማሽከርከር ተገቢ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው፡፡

## በአልኮል መጠጥ የተመረዘ አሽከርካሪ ሲያጋጥሞት ማድረግ ያለብዎት ክንዋኔ

- በአልኮል መጠጥ ተመርዘው የሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች በተመለከቱ ወቅት አሽከርካሪ ዎቹን ላለመጠጋት ጥረት ያድርጉ፡፡ ምክንያቱም ሰክረው የሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች የራሳቸውን ህይወትና የሌላውንም ህይወት አደጋ ውስጥ ሊጨምሩ ስለሚችሉ ነው፡፡ ስለሆነም ከመጠጋት ይልቅ ለፖሊስ ደውለው ማሳወቅ ይመረጣል፡፡
- በአንዳንድ ሃገሮች የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በአልኮል መጠጥ ተመርዘው የሚያሽከርክሩ አሽከርካሪዎች የሚበዙት ከምሽቱ 4:00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 8:00 ሰዓት ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ወቅት በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ከወትሮ የተለየ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

# ሞገደኝነት/የክልፍልፍ/ አነዳድ

- በተደጋጋሚ በመጥፎ እና በተረበሸ ስሜት ውስጥ ሆኖ የማሽከርከር ውጤት ነው፡፡

# ሞገደኛ አሽከርካሪዎች

- በአልኮል መጠጥ ተመርዘው ያሽከረክራሉ
- በአደንዛዥ እጽ ወስደው ያሽከረክራሉ
- በንዴት ስሜት ውስጥ ሆነው ያሽከረክራሉ
- በሀዘን ስሜት ውስጥ ሆነው ያሽከረክራሉ
- በጭንቀት ስሜት ውስጥ ሆነው ያሽከረክራሉ
- በፍርሀት ስሜት ውስጥ ሆነው ያሽከረክራሉ
- በማሽከርከር ወቅት አትኩሮት በሌላ ነገር ሲወሰድ

# የሞገደኛ አሽከርካሪዎች የአነዳድ ባህሪዎች

1. የትዕግስት ማጣትና የትኩረት አለመስጠት
2. ተጽዕኖ የማድረግ ትግል
3. ግዴለሽነትና የመንገድ ዳር ጸብ

# ሞገደኛ አሽከርካሪ ላለመሆን መደረግ ያለባቸው ተግባራቶች

- በተረበሹ፤ በተበሳጩ፤ በተቆጡ ወቅትና ይህን መሰል ስሜት ውስጥ ሲሆኑ አለማሽከርከር
- የሚያሽከረክሩት ከተማ ውስጥ ከሆነ የጉዞ ሰዐትን ከስራ መግቢያና መውጫ ሰዐት ውጪ ማድረግ
- መኪና ውስጥ ያለን ምቾት ማሻሻል
- ለስላሳ ሙዚቃ ድምጹን ዝግ አድርጎ ማዳመጥ
- ስሜትን መቆጣጠር ፡ ሞገደኛ አሽከርካሪ ሲያጋጥም ከመበቀል መቆጠብ
- ለሌሎች ቅድሚያ መስጠት፤ ጨዋ መሆን፤ ለሰው ልጅ ክብር መስጠትና ይቅር ባይ መሆን

# ሞገደኛ አሽከርካሪ ሲያጋጥምህ

- የፉክክር ስሜት ውስጥ አለመግባት
- ጺያፍ ስድቦችን ችላ ማለት
- የአይን ለአይን ግንኙነትን ማወገድ

# የማሽከርከር ባህሪያት ዘርፎች

# 1. የስሜት ባህሪ

- ፍላጎት፤አመለካከት፤እሴትና መነሳሳት ማንኛውንም ስሜት ያጠቃልላል፡፡

## 2. የመገንዘብ/የአእምሮ/ባህሪ

- መረዳት፤ማሰብ፤ምክንያት፤ውሳኔ መስጠትና የሰዎችን ድርጊት ማጤንን ያጠቃልላል፡፡

# 3. የክህሎት ባህሪ

- በአዕምሮ አዛዥነት በአካል እንቅስቃሴ የሚፈጸም ማናቸውም የክህሎት ባህሪያትን ያጠቃልላል፡፡

# ጠንቃቃ የማሽከርከር ሂደትን ለማከናወን መነሳሳት

- የመጀመሪያ ደረጃ ጥንቃቄ መሚደግፉ ወይም የሚያነሳሱ እሴቶችና ስሜቶችን በንቃት መተግበር ነው፡፡

እሴቶች

- አሽከርካሪው በንቃት ለማሽከርከር የሚተልባቸው መሰረታዊ መርሆች ናቸው፡፡የማሽከርከር ስነ-ባህሪ መሰረታዊ እሴቶች ኃላፊነት፤ደህንነት/ጥንቃቄና ብቃት በመባል ይታወቃሉ፡፡

# ሀ.ኃላፊነት

የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያበረታታ እሴት ክፍል ነው፡፡

- ለሌሎች ማሰብና ስነ-ምግባራዊነትን መላበስ
- አዎንታዊ ህሊናዊ አስሳሰብ
- ደስተኝነትና እርካታ

## ለ. ደህንነት/ጥንቃቄ

የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያበረታታ እሴት ክፍል ነው፡፡

- ራስን ማዘጋጀትና ሚዛናዊትን/የእኩልነት ስሜት
- ሚዛናዊ የውሳኔ አሰጣጥ
- ትህትና ተላብሶ መግባባትና የመረጋጋት ስሜት

# ሐ. ብቃት

የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያበረታታ እሴት ክፍል ነው፡፡

- ደንብን ማክበርና ልበ-ሙሉነት
- እውቀትና ግንዛቤ ማዳበር
- ትክክለኛ ተግባርና ጠንቃቃነት/ንቁነት

# በመከላከል ላይ የተመሰረተ የአነዳድ ባህሪ መርሆች

- አደጋን ተከላክሎ የማሽከርከር መርሆች አሽከርካሪው በራሱ ተነሳሽነት አደጋ ሳያደርሱ ማሽከርከር የሚችሉባቸው ሂደቶች ናቸው፡፡በዚህም መሰረት አሽከርካሪው የራሱን የማሽከርከር ስርዐት ዘወትር በማረምና በመከታተል መልካም የአነዳድ ባህሪ የሚያዳብሩበትን የተለያዩ ደረጃዎች ያለው አካሄድ፡፡
- ደረጃ አንድ መጠንቀቅ፡- አሽከርካሪው አሉታዊ ልምድ አለብኝ ብሎ የማሽከርከር ተግባሩን የሚረዳበት ነው፡፡
- ደረጃ ሁለት መመስከር፡- አሽከርካሪው አሉታዊ የሆነ የማሽከርከር ስራዎችን ሲፈጽሙ በራሱ ላይ የሚመሰክርበት ነው፡፡
- ደረጃ ሶስት መቀየር/ማሻሻል፡- አሽከርካሪው አሉታዊ የማሽከርከር ተግባር ለማረም የሚወስደው ተግባራዊ እርምጃና የሚያመጣው የባህሪ ማሻሻል ነው፡፡

# የመልካም አሽከርካሪ ባህሪያትን ለማዳበር የሚጠቅሙ አካላዊና ስነ-ልቦናዊ እውነታዎች

- የመንገድ ላይ ትህትናን መላበስ
- ከሌሎች አካላት ወይም የመንገድ ተጠቃሚዎች ጋር የሚፈጠር ግጭት መከላከልና መቆጣጠር
- ጤናማ የእርስ በእርስ ግንኙነት መገለጫዎችን ማደበር

  **መቻቻል፤-** ባይፈልጉም/ባይስማሙበትም ለጊዜው ፈቃደኝነትን ማሳት

  **ማካፈል፡-** የራስ ነገር ሌላው እንዲጠቀምበት መፍቀድ

  **ሩህሩነት፤-** የሌሎችን ችግር እንደራስ መመልከት

  **መደራደር፡-** ለመግባባት ሲባል መጠነኛ የራስ ፍላጎትን መተው፡፡

- የማሽከርካሪ ስነ-ምግባር/መመሪያ/ በተግባር መተርጎም

# የትራፊክ አደጋ መነሻ የሚሆኑ ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች

ሀ. ውስጣዊ ምክንያቶች

- እድሜ
- ጤና
- አልኮል
- ጫትና አደንዛዥ እጽ
- የድካም ስሜት

# ለ. ውጫዊ ምክንያቶች

- ኢኮኖሞያዊ ቀውስ
- ስነ-ልቦናዊ ቀውስ
- ማህበራዊ ችግር

Thank you